<u>እውን ኦነግ አቋሙን ቀየረ?</u>

ከአህመድ ይማም

አንድ ሕብረብሄራዊ የሆነ ድርጅት በዕለቱ አንድ አውሮፓዊ ከተማ ውስጥ ስለአካሄደው ህዝባዊ ስብሰባ ነበር የፓልቶኳ እመቤት የሚናገሩት። ሴትዮዋ የድርጅቱን መሪ ስም ጠቀሱና ግለሰቡ ወደስብሰባ ሲገባ ለታዳሚዎቹ "አሁን ወደስብሰባ ልገባ ስል አንድ የሚያስደስት የኢሜል መልዕክት አገኘቻለሁ። ... ተጣልተው በነበሩት የኦነግ ወገኖች መካከል እርቅ ወርዷል። ..." ማለቱን ሲናገሩ ሰማሁዋቸው። ፓልቶኩ የሚባለው ግለሰብ የሚመራው የፖለቲካ ድርጅት ጠንካራ ደጋፊ መሆኑን ስለማውቅ የሴትዮዋን ንግግር አልተጠራጠርኩትም። (ሁዋላም ስብሰባው በተካሄደበት ከተማ ከሚኖሩ ወዳጆቼ እንዳጣራሁት ያሉት ነገር እውነት ነው) በኢትዮጵያዊነት ለተጠራው ታዳሚ የምስራች ተብሎ ከተነገረው የኦነግ እርቅ ጋር፣ ለኢትዮጵያ ጠቃሚ የሆነ ምን አስደሳች ለውጥ በድርጅቱ ውስጥ ተከስቶ ይሆን አልኩና እራሴን ጠየቅሁ።

አሁን ጊዜ ሁሉም ድርጅት ማለት ይቻላል ድረ-ገፅ አላቸው- በልሳንነት የሚጠቀሙበት። ሰውም መጠየቅ አላስፈለገኝ። ጠቆምኩት ኮምፒተሬን። በኦነግ ውስጥ ምንም የአቋም ለውጥ የለ።

ይህ ከዚህ በታች የሰፈረው **ከሀበሻ ቅኝ አገዛዝ ነጻ ለመውጣት** ነው ትግላችን የሚለው የኦነግ አቋም አሁንም የድርጅቱ ልሳን በሆነው ድረ ገጽ ላይ ሰፍሮ ያለ ነው።

"***The Oromo Liberation Front (OLF) is a political organization established in 1973 by Oromo nationalists to lead the national liberation struggle of the Oromo people against the Abyssinian colonial rule. The emergence of the OLF was a culmination of a century old yearn of the Oromo people to have a strong and unified national organization to lead the struggle.***"

የፓልቶኳ እመቤት ይናገሩ የነበረው ስለዶክተር ብርሃኑ ነበር። ታዲያ በሰሞኑ ዶክተር ብርሃኑ አቅዋም ቀይረዋል እንተቃቀፋቸው እያለ የሚናገረው ከየት የመጣ ነው? ምን መሰረት አለው? ብዙ ጥያቄዎችን ለራሴ አሰላሰልኩና ከአንባቢያኔ ሃሳቤን ልጋራ አሰብኩ። ባለው ተጨባጭ መረጃ፣ ከኦነግ ጋር በፍቅር የሚያዳራ ምንም መሰረት የለውም። የዶክተሩ ኦነግ ኦነግዬ ከበሮ ድለቃ ለብዙሀኑ የሚገባ አይደለም።

ኦነግ ማነው? ማን ያውራ ያወቀ ነውና ስለዚህ ድርጅት አነሳስ ዶክተር መረራ በበቂ መረጃ ሰጥተውናል። በወለጋ ሚስዮናውያን ተጠምቀው ከተቋቋሙ ጀምሮ ከሀገር አንድነት አንጻር ያደረሱት ጉዳት ዛሬም አብሮን ያለ ነው።

**ኦነግ በምን ይታወቃል?**

- ከምስረታው ጀምሮ ኦሮሞዎች ኢትዮጵያዊ አይደለንም የአማራ ቅኝ ተገዢ ነን በማለቱ፤
- በሻዕቢያ ተረድቶ ዋና መለያው ጸረ አማራ፤ ጸረ ኢትዮጵያ አንድነት እንቅስቃሴ በማካሄዱ፡
- ሁኔታው ሲያመች ግን ከመጣው አገዛዝ (ደርግ ሆነ ወያኔ) ጋር መተባበሩ፤ የደርግ ቀበሌና ከፍተኛና አብዮት ጥበቃ መዋቅር አካል መሆኑ፡
- ሌሎች ተቃዋሚ ሃይሎችን በተለይም ህብረብሄራዊ የሆኑትን ባገለለ ሁኔታ ከወያኔ ጋር ተቃቅፎና የቀረበለትን ሀገር አፍራሽ ህገ-መንግሥት አጨብጭቦ በማፅደቁ፣
- አመራሩ በመለስ ከሀገር የመውጫ ቪዛ ሲሰጠው በርካታ አባላቱን አሲይዞ በመውጣቱ፡
- በበደኖ አማራዎችን በግፍ በመግደሉ፡ (እዚህ ላይ የክርስትና እምነት ተከታይ በመሆናቸው ብቻ አማራ ተብለው ኦሮሞዎችን ጨምሮ የሌሎችም ብሄረሰቦች አባላት መገደላቸውን ያስታውሷል)
- ቀደም ሲል በሻዕቢያ ታግዞ በአሶሳ ብዙ መቶዎች ኣማራዎችን በአስቃቂ መንገድ በመጨረሱ፤
- በሞያሌ ኬንያ አክባቢ ሀገር ገብተው ጸረ ወያኔ ተልዕኮ ሊፈጽሙ ያሉ ዜጎችን ይዞና አፍኖ በመግደሉ፤
- የሻዕቢያ መሳሪያ በመሆኑ፤
- ነጋ ጠባ ኢትዮጵያዊ አይደለሁም በማለቱና ነፃ ኦሮሚያን እመስርታለሁ በማለቱ ነው ኦነግ የሚታወቀው።

የዶክተር ብርሃኑ ለኢትዮጵያ አሳቢ ኦነግ በሕዝብ አይታውቅም። በዚያድ ባሬ ጀኔራል የሚመራው የኦጋዴን ነፃ አውጪ ግንባርም ኦጋዴንን እገነጥላለሁ ሲል እንጂ ኢትዮጵያዊ ነኝ ሲል ተሰምቶ አያውቅም። ዶክተር ብርሀኑ ታዲያ ያልሆነን ነገር ሆነ ብሎ ለምን ያደናግረናል? ማንን ሊጠቅም?

**ኦነግ እውን አቋሙን ከቀየረ ማድረግ ያለበት ቀላል ነው። ዶክተር ብርሀኑንም የሰይጣን ጠበቃ አድርጎ ማጋለጥና በአጣብቂኝ መክተት የለበትም።**

- ኦነግ እውን ኢትዮጵያዊ ነኝ ካለ ቅኝ ተገዢ ነን የሚለውን በይፋ ይሰርዛል፤
- የኢትዮጵያ ታሪክ መቶ ዓመት አይሞላውም የሚለውን ከአውነት የራቀ ቅስቀሳውን ያቆማል፤
- ጸረ አንድነት ሀይሎች እንቅስቃሴውን ያሳርፋል፤

ኦነግ ባለው ይዞቱ የኢትዮጵያ አንድነት ፀር ነው። ኦነግ ተባባሪ ብለው እሰየው ያሉት እነ ዶክተር ብርሀኑ ሰልፋችው ከወዬት ነው መባሉ ትክክል የሆነው ለዚህ ነው። ችግራቸው የንቃት ማነስ ነው? የቀቢያ ተስፋ? ራሳችው በጎጠኝነት መበከል? ሁሉም ጥያቄ ተገቢ ነው።

ኦነግ በሕዝብ ላይ ለፈጸማቸው ወንጀል አጠፋሁ ሲል አልተደመጠም። በአሶሳና በደኖ፣ በምስራቅ ወለጋ ወዘተ የፈሰሰው ደም  የአማራ ስለሆነ ነው ለነ ዶክተር ብርሃኑ ያልቆጠቆጣቸው?  ብዙ ጥያቄዎች ያስነሳል የእኛ ነገር።

የእኛ ነገር "ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጣል" እየሆነብኝ ነው።  እኛ ስል የኢትዮጵያ አንድነት ደጋፊውን ወገን ማለቴ ነው።  በተለይም በባዕድ ሀገር ያለው።  በቁጥር ብዙሃኑ ወገን እንደሆን አምናለሁ።  ግና ሥራችን ሁሉ አድሮ ጥጃ እየሆነ ነው ልበል?

ከትላንት ወዲያ ወያኔን ግፋ በለው አልን።  ጥቂት የጨለማ መቅረዞች ደርግም ወያኔም ሀገር አጥፊዎች ናቸው፣ ተባብረን ዘላቂ ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ እናምጣ ሲሉን፡ '… ጠርነት ወዳዶች፣ ጠርነት ናፋቂዎች … ከደርግ የባሰ አይመጣም …ወዘተ አልናቸው።  አንዳንዶቻችንም "ልጆቻችን … ወዘተ" በሚሉት ማሞካሻዎች አጅበን ለንዋዛቸው ሞከርን።  የተፈራው አልቀረም።  የወያኔ ጭራቅነት በራችንን ሲያንኳኳ ወይም ጊዜ አስተምሮን ተቃዋሚ ሆን።  ግና አሁንም ደግሞ ወያኔን ጨምሮ ፀረ-ኢትዮጵያ ሃይሎች ጨዋታውን በእኛ ሜዳ ላይ ነው እያካሄዱ ያለው።  ኳስ አበደች ጨዋታውን እያካሄዱ ያለው በእኛው በአፍቃሪ የኢትዮጵያ አንድነት ጎራው ሜዳ ውስጥ ነው።

በስም ካልሆነ በተግባርና በዓላማ ከወያኔ የማይለዩትን የመለስ ተቃዋሚ ሁሉ ግፋ በለው እያልን ዓለምአቀፋዊ ዕውቅናና ድጋፍ እንዲያገኙ፣ በታሪክና በሀገር መፃኢ ዕድል ላይ መርዛማ እሾሃቸውን እንዲዘሩ እንረዳለን። ስለአንድነት ሃይሎች እንቅስቃሴ አይበርደንም፣ አይሞቀንም።  ጉዳታቸው

አያመንም፣ አይቆጨንም። እድገታቸው አያስደስተንም፣ አያስፈነቅደንም። አንዳንድ ጊዜ እንደውም በሾኬ ልናደናቅፋቸው እናደባለን። እስኪ ላፍታ አንዳንድ ጥያቄዎችን ለራሳችን እናቅርብ፡

- ላለፉት ሃያ ዓመታት ሁሉም በየቋንቋ መንደሩ በሩ ተዘግቶበት፣ የየራሱ ዓርማና መንግሥታዊ ተቋማት ተሰርተውለት፣ በኢትዮጵያዊነት የሥነ-ልቦና ህብቱና ትስስሩ ላይ ጎጠኝነት እንዲያደራበት እየተደረገ ባለበት የሀገራችን ሁኔታ ከኢትዮጵያ እንገንጠል ባይ ሃይሎች መጠናከራቸው በምን ሥሌት ነው የሚጠቅመን?
- ሀገራችንንና ህዝባችንን ወደዬት ነው ልንወስዳቸው የምንሻው?
- አንድነቷ የተጠበቀ፣ የሕዝቧ የሀገርና የሥልጣን ባለቤትነት የተረጋገጠባት ወይስ እንገንጠል ባይ ሃይሎች ቅርጫ አስገብተው የሚቧጨቋት ኢትዮጵያን ነው ለማየት የምንመኘው?

አንድ ሰው ጅብ ላሙን ሊበላበት ሲል ቢያገኝ፣ ከመጀመሪያው ጅብ በማስጣል ለሌላ ጅብ አሳልፎ የሚሰጥ አይመስለኝም። እኛም ከዘረኛው ወያኔ ወደሌላ ዘረኛ ቡድን/ቡድኖች ለማሸጋገር አይመስለኝም ለኢትዮጵያ ያለን ህልም። ህልማችንና ድርጊታችን ግን ፍዬል ወዲያ፣ ቅዝምዝም ወዲህ እየሆነ ስለሚመስለኝ፣ ቆም ብለን እራሳችንን መመርመር እንዳለብን ይሰማኛል። ጥንት ነበር እንጅ መጥኖ መደቆስ፣ አሁን ምን ያደርጋል ድስት ጥዶ ማልቀስ እንዳይሆን። በፖሊተካው መስክ የምናደርገው እንቅስቃሴ በሀገርና በወገን መጭ ዕድል ላይ የየራሱ አዎንታዊ/አሉታዊ አስተዋፅኦ ስለሚኖረው፣ ድጋፋችንንም ቢሆን እንደ እግር ኳስ ቡድን ድጋፍ አቅለን ልናየው የሚገባ አይመስለኝም።

የኦነግ፣ የኦነአግ (የዚያድ ባሬ ባለአምስት ኮከብ — አንዱ ኦጋዴን ይወክላል — ዓርማው፣ የዚያድ ባሬ ከፍተኛ የጦር መሪ መሪው) ወዘተ ሀገር ገንጣይ እንቅስቃሴዎችን ገድል በማዳነቅ የሚዘግቡልንን ድረ-ገፆችና ሌሎች የህዝብ መገናኛዎችን እየረዳን እናዳንቃለን። ከብርሃን በፈጠነ ሁኔታ የነኦነግን እንቅስቃሴ የሚዘግቡት እነኝሁ ድረ-ገፆች፣ የአንድነት ሃይሎች ምን በጎ ነገር

ቢሰሩ ትንፍሽ ሳይሉ ሲቀሩ ለምን ብለን አንጠይቅም። "ያልጠረጠረ ተመነጠረ" የሚለው የቆዬ አባባል በተቢው ቦታ ጠቀሜታ እንዳለው እረስተናል። በራሳችን ለራሳችን በምናዘጋጃቸው መድረኮች — ስብሰባዎች፣ ሰልፎች ወዘተ — እንገንጠል ባዮቹን እየጋበዝናቸው ከታሪክ የተጣላና ደም ያረገዘ ፀረ-ኢትዮጵያ ግባቸውን እንዲደሰኩሩ፣ ስለፍትሃዊነቱና ተገቢነቱ እንዲሰብኩ እናበረታታለን። አውቀነውም ሆነ ሳናውቀው ኢትዮጵያን የማፈራረስ ህልማቸው እውን እንዲሆን ድጋፋችንን እንሰጣለን። "ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጣል" ከሚለውም በባሰ "ከሞኝ ደጃፍ ዛፍ ከሥሩ ተነቅሎ ይወሰዳል" እንዲሉ። አለን የምንለው ህልም ሌላ፣ የምንሄድበት መንገድ የሚያመራው ወደሌላ።

እያስተዋልን እንጅ ጎበዝ! ከዛሬ 65 ዓመት በፊት፣ ሮም ላይ ኢትዮጵያዊ የአርበኝነት ገድሉን ለማከናወን በልቡ ሰንቆ ሳለ፣ ለወንድሙ ለተስፋጽዮን በፃፈው ደብዳቤ፥

"... አባቶቻችን በምሳሌ ሲሰድቡ 'መሬት ሲያረጅ መጭ ያበቅላል' ይላሉ። እነሱ በኩራትና በክብር፣ በደማቸውና በአጥንታቸው የገነቡትን ነፃነት እኛ ዛሬ እንሻሻጥበታለን። ያሳዝናል! ... " ያለው ዘርዓይ ደረስ ዛሬ ቀና ብሎ ለመታዘብ ቢችል ምን ይል ይሆን?